# የኢትዮጵያ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች አትሌቲክስ ሻምፒዮና

# ሕግና ደንብ

## የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን

የካቲት 26 እስከ መጋቢት 01/2011 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

# የኢትዮጵያ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች አትሌቲክስ ሻምፒዮና

# አጠቃላይ መረጃ

- የውድድሩ ቀን፡- የካቲት 26- መጋቢት 01/2011 ዓ.ም.
- የውድድሩ ቦታ፡- አዲስ አበባ ስታድየም
- የውድድሩ ተሳታፊዎች፡- ክልሎችና፣ከተማ አስተዳደሮች
- አዘጋጅ፡- የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን

## አድራሻ

- ፖ.ሣ.ቁ 13336
- ፋክስ 251-11-6450879
- ኢ-ሜል eth@mf.iaaf.org
- Website www.eaf.org.et
- ☎ 251-11-6479579<br>251-11-6479676<br>251-11-6479596<br>251-11-6479131<br>***ጉርድ ሾላ***<br>***አዲስ አበባ***

## ጥቅል ኘሮግራም

- *የካቲቲ 25/2011 ዓ.ም. የቴክኒክ ስብሰባ ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት አዲስ አበባ ስታድየም፤*
- *የካቲት 26-መጋቢት 01/2011 ዓ.ም. ውድድሩ የሚካሄድበት ቀን፤*

# ፲ኛዉ የኢትዮጵያ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች አትሌቲክስ ሻምፒዮና

# ሕግና ደንብ

**ዓላማ፡ -**

1. በክልሎች፣ በከተማ አስተዳድሮች ለሚገኙ አትሌቶች የውድድር ዕድል ለመፍጠር፤
2. ተተኪ አትሌቶችን ለማፍራት፤
3. ክልልና ከተማ አስተዳደሮች የሥልጠና ውጤታቸውን መለካት ለማስቻል፤

## *አንቀጽ አንድ*

## *አጠቃላይ የውድድሩ ደንብ*

1. **የውድድሩ መጠሪያ፡-** ይህ ውድድር የኢትዮጵያ ክልሎችና ከ/አስተዳደሮች አትሌቲክስ ሻምፒዮና ተብሎ ይጠራል፡፡
2. **ውድድሩ የሚመራው፡-** በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽንና በIAAF ውድድር ህግና ደንብ መሠረት ይመራል፡፡
3. **ውድድሩን በበላይነት የሚመራ አካል፡-** የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ነው፡፡
   - **የውድድሩ አግባብነት፡-** በአንድ የውድድር ተግባር ሁለት ቡድኖች፣ ሦስት እና ከሦስት በላይ አትሌቶች ተመዝግበው ለውድድር ከቀረቡ ውድድሩ ይካሄዳል፡፡ ከዚህ በታች ከሆነ ግን ከቀጣይ ውድድሮች እንደ አስፈላጊነቱ ሊታገድ ይችላል፡፡
   - ውድድሩ በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በሚያስመዘግቡት ውጤት መሠረት ለአሸናፊዎች የሜዳሊያና የዋንጫ ሽልማት ይሰጣል፡፡
4. **የተወዳዳሪ ተገቢነት፡-**

4.1 በውድድሩ የሚሳተፉ አትሌቶች በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በማህተም የተረጋገጠና የስም ዝርዝራቸው ከደንቡ ጋር በተላከዉ ቅፅ መሰረት የተመዘገቡ አትሌቶች ብቻ ናቸው፡፡

**4.2 በውድድሩ የማይሳተፉ አትሌቶች፡-**

4.2.1 በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ያሉ ማንኛውም ክለብ፤

4.2.2 የኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ፣ የጥሩነሽ ዲባባ ማሠልጠኛ ማዕከል ውስጥ እየሰለጠኑ ያሉ ሠልጣኞች፤

4.2.3 በማንኛውም ጊዜ በብሔራዊ ቡድን የተመረጡ እና፣

4.2.4 የውጭ ሃገር የውድድር እድል ያገኙ አትሌቶች በዚህ ውድድር መሳተፍ አይችሉም፤

## *አንቀጽ ሁለት*

## *የውድድሩ ቀንና ቦታ*

የኢትዮጵያ ክልሎችና ከ/አስተዳደሮች አትሌቲክስ ሻምፒዮና የካቲት 26 እስከ መጋቢት 01/2011 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ስታድየም ይካሄዳል፡፡

## አንቀጽ ሦስት

## የውድድሩ ዕድሜ

1. በዚህ ውድደር የሚካፈሉ ታዳጊ አትሌቶች ማለትም ዕድሜያቸው 16 ወይም 17 ዓመት የሆኑ አትሌቶች /1994-1995 ዓ.ም. / ወይም /እ.ኤ.አ 2002-2003/ የተወለዱ በውርወራ ተግባራት፣ በ10,000 ሜትር፣ በእርምጃ ውድድሮች መሳተፍ አይችሉም፡፡ ነገር ግን በሌሎች የውድድር ተግባራት መሳተፍ ይችላሉ፡፡
2. ዕድሜያቸው ከ16 ዓመት በታች የሆኑ አትሌቶች /በ1996 ዓ.ም. /እ.ኤ.አ በ2004/ የተወለዱ በዚህ ውድድር መካፈል አይችሉም፡፡

## አንቀጽ አራት

## በውድድር መሳተፍ

አንድ አትሌት በሦስት የግል እና በአንድ የቡድን (ድብልቅ ሪሌ) ብቻ መሳተፍ ይችላል፡፡

## አንቀጽ አምስት

## ምዝገባ

1. የምዝገባ ጊዜ የካቲት 05-14/2011 ዓ.ም. ድረስ ይሆናል፡፡ ከላይ በተጠቀሰው የምዝገባ ጊዜ ገደብ ውስጥ ያልተመዘገበ ቡድን ብር 300 (ሶስት መቶ ብር) በመክፈል የካቲት 15/2011 ዓ.ም እስከ ቀኑ 6፡30 ብቻ መመዝገብ ይችላል፡፡
2. ማንኛውም ተሳታፊ ቡድን በየውድድር ተግባሩ ከነተጠባባቂው አራት አትሌቶችን ማስመዝገብ ይችላል፡፡
3. ለድብልቅ ሪሌ እያንዳንዱ ቡድን ከአራት እስከ ስድስት አትሌቶች ማስመዝገብ ይችላል፡፡
4. ክልሎች፣ ከተማ አስተዳደሮች የተሳታፊዎችን ስም ዝርዝርና ሌሎች መረጃዎች ከዚህ ደብዳቤ ጋር ተያይዞ በቀረበው ቅጽ መሠረት ብቻ ሞልተው መላክ አለባቸው፡፡ የተወዳዳሪዎች ዝርዝር የትውልድ ዘመን ማካተት አለበት፡፡

## አንቀጽ ስድስት

## የውድድር ዓይነት

በ1ኛዉ የኢትዮጵያ ክልሎችና ከ/አስተዳደሮች አትሌቲክስ ሻምፒዮና ከዚህ የሚከተሉት ዉድድሮች ይካሔዳሉ፤

| ለሴቶች | የውድድሩ ተግባራት | የወንዶች |
|---|---|---|
| ✓ | 100 ሜትር | ✓ |
| ✓ | 200 ሜትር | ✓ |
| ✓ | 400 ሜትር | ✓ |
| ✓ | 800 ሜትር | ✓ |
| ✓ | 1500 ሜትር | ✓ |
| ✓ | 5000 ሜትር | ✓ |
| ✓ | 10,000 ሜትር | ✓ |
| - | 110 ሜ. መሠናክል | ✓ |
| ✓ | 100 ሜ. መሠናክል | |
| ✓ | 400 ሜ. መሠናክል | ✓ |
| ✓ | 3000 ሜ. መሠናክል | ✓ |
| ✓ | አሎሎ ውርወራ | ✓ |
| ✓ | ዲስከስ ውርወራ | ✓ |
| ✓ | ጦር ውርወራ | ✓ |
| | መዶሻ ውርወራ | ✓ |
| ✓ | ከፍታ ዝላይ | ✓ |
| ✓ | ርዝመት ዝላይ | ✓ |

| | | |
|---|---|---|
| ✓ | ሱሉስ ዝላይ | ✓ |
| ✓ | ምርኩዝ ዝላይ | ✓ |
| ✓ | 20 ኪ.ሜ. እርምጃ | ✓ |
| ✓ | 4X100 ሜትር | ✓ |
| ✓ | 4X400 ሜትር | ✓ |

## *አንቀጽ ሰባት*

## *የተወዳዳሪ ቅያሪ*

1. ማንኛውም ክልል/ከ/አስተዳደር በየውድድር ተግባሩ በየቀኑ የተወዳዳሪ ለውጥ ማድረግ ከፈለገ ቀጣይ ውድድር ከመደረጉ ከአንድ ቀን በፊት እስከ ቀኑ 4፡00 ሰዓት ለውድድሩ ከተመዘገቡት አትሌቶች ውስጥ ለቅያሪ በተዘጋጀው መቀየሪያ ቅጽ አትሌቶችን በማስመዝገብ የውድድሩ ቴክኒካል መረጃ ክፍል (TIC) ማቅረብ አለበት፡፡ የተወዳዳሪዎች ቅያሪ የሚደረገው በየውድድር ተግባራቱ ከተመዘገቡት አራት አትሌቶች ብቻ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ከተጠቀሰው ሰዓት ውጭ ለሚቀርበው የተወዳዳሪዎች ቅያሪ ጥያቄ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡
2. በዱላ ቅብብል የተወዳዳሪዎች ጥንቅርና የአሯሯጥ ቅደም ተከተል ምዝገባ የሚካሄደው ለዱላ ቅብብል ውድድር የስም ጥሪ ከመደረጉ ከአንድ ሰዓት በፊት ለቴክኒካል መረጃ ክፍል ማሳወቅ ያስፈልጋል፡፡
3. ለዱላ ቅብብል ከተመዘገቡት ከማንኛውም የውድድር ተግባራት ቀይሮ ማወዳደር ይቻላል፡፡ ይኸውም ለመጀመሪያ ዙር ውድድር ብቻ ይሆናል፡፡ ነገር ግን በቀጣይ ዙር ውድድሮች መቀየር የሚቻለው ለዱላ ቅብብሉ ከተመዘገቡት ሁለት አትሌቶች ብቻ ይሆናል፡፡

## *አንቀጽ ስምንት*

## *በውድድሩ ላይ የሚሳተፉ አትሌቶችን ማሳወቅ /Final conformation/*

ተወዳዳሪ ቡድኖች በእያንዳንዱ የአትሌቲክስ ተግባራት የሚመወዳደሩትን አትሌቶች በቅደም ተከተላቸው መሠረት የመጨረሻ ምዝገባ በቴክኒካል ስብሰባ ቀን የካቲት 25/2011 ዓ.ም./ /Final conformation/ ያደርጋሉ፡፡

ከመጨረሻ ምዝገባ በኋላ ሌሎች አትሌቶችን ቀይሮ ማወዳደር አይቻልም፡፡ ነገር ግን በሚቀርበው ሕክምና ማስረጃ መሠረት አትሌቶችን ቀይሮ ማወዳደር ይቻላል፡፡

## *አንቀጽ ዘጠኝ*

## *የአትሌቱ ጤንነት*

በውድድሩ ተካፋይ የሚሆን አትሌት ጤናው የተሟላ መሆን አለበት፤ ጤናው ያልተሟላ አትሌት በውድድሩ ተሳትፎ ቢገኝና ጉዳት ቢደርስበት ተጠያቂ የሚሆነው ክልሉ/ከተማ አስተዳድሩ ወይም አትሌቱ ይሆናል፡፡

## *አንቀጽ አስር*

## *ውጤትን ስለመግለጽ*

1. የዕለቱ ውድድር ውጤቶች ለተወዳዳሪዎችና ለቡድኖች በየውድድሩ ጣልቃ በማስታወቂያ ሠሌዳ እና በውድድር ፍፃሜ በኮሚኒኬ ይገለፃል፡፡

2. በተገለጹት ውጤቶች ላይ ስህተቶች ካሉ ወዲያውኑ የቡድን መሪው/አሠልጣኝ የውድድሩ ቴክኒካል መረጃ ክፍል (TIC) በመቅረብ የማስተካከያ ጥያቄ ማቅረብ ይቻላል፡፡
3. ከውድድሩ ቴክኒካል መረጃ ክፍል (TIC) የውድድሩ ውጤት ይፋ ሳይደረግ ውጤቱን ለህዝብ መግለጽ የተከለከለ ነው፡፡

## *አንቀጽ አሥራ አንድ*
## *ክስና ይግባኝ ስለማቅረብ*

1. የአትሌት ተገቢነት የክስ ጥያቄ ማቅረብ የሚቻለው ቢያንስ ውድድሩ ከመጀመሩ ከ30 ደቂቃ በፊት ነው፡፡
2. የውድድር ውጤቶችን ወይም የውድድር ተግባር ሁኔታን በተመለከተ የክስ ጥያቄ የሚቀርበው ውጤቱ ይፋ በሆነ በ30 ደቂቃ ጊዜ ውስጥ ነው፡፡
3. ማንኛውም የክስ ጥያቄ መጀመሪያ የሚቀርበው ለውድድሩ ዋና ዳኛ (refree) በቃል በአትሌቱ፣ በአሠልጣኙ ወይም በቡድን መሪው አማካይነት ሊሆን ይችላል፡፡ የውድድሩ ዋና ዳኛው ውሳኔ መስጠት ወይም ጉዳዩን ለይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ሊያቀርብ ይችላል፡፡
4. በዋና ዳኛው ውሳኔ ያልተስማማ አካል በጽሑፍ ከብር 300.00 (ሦስት መቶ ብር) ጋር ለይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ዋና ዳኛው ውሳኔ በሰጠ በ30 ደቂቃ ውስጥ ክስ ማቅረብ ይችላል፡፡
5. ክሱ በክስ ሰሚ ኮሚቴ ተጣርቶ ተገቢ ክስ ሆኖ ከተገኘ የተያዘው ብር ተመላሽ ሆኖ ክሱ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡ ክሱ ተቀባይነት ካላገኘ የተያዘው ገንዘብ ለፌዴሬሽኑ ገቢ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ክሱ ተቀባይነት ካላገኘ የተያዘው ብር ለፌዴሬሽኑ ገቢ ሆኖ ውሳኔው የፀና ይሆናል፡፡ ውሳኔውም የመጨረሻ ይሆናል፡፡

## *አንቀጽ አስራ ሁለት*
## *አለባበስ*

1. ማንኛውም ተወዳዳሪ የክልሉን ወይም የከተማ አስተዳደሩን መለያ የሆነውን የስፖርት ትጥቅ መልበስ አለበት፤ መለያ ለብሶ ያልቀረበ ተወዳዳሪ መወዳደር አይችልም፤
2. ማንኛውም የሜዳሊያ ተሸላሚ አትሌት የክልሉን ወይም ከተማ አስተዳደሩን መለያ የሆነውን የስፖርት ልብስ ለብሶ ለሽልማት መቅረብ አለበት ይህ ካልሆነ ሽልማት አይሰጠውም፡፡

## *አንቀጽ አስራ ሦስት*
## *የመወዳደሪያ መሮጫ ቁጥር*

ማንኛውም ተወዳዳሪ አትሌት የመወዳደሪያ ቁጥር ሊኖረው ይገባል፣ ቁጥሩ የሚለጠፈው ግልጽ ሆኖ በሚታይ ቦታ በደረትና በጀርባ ላይ ነው፡፡ የምርኩዝ ዝላይና የከፍታ ዝላይ ተወዳዳሪዎች አንድ የመወዳደሪያ ቁጥር ብቻ በደረት ወይም ከጀርባ ላይ ለጥፎ መወዳደር ይቻላል፡፡ በሪሌ ውድድር ከጀርባ ቁጥር በተጨማሪ አትሌቱ የክልሉን ወይም ከተማ አስተዳደሩን ስም የሚገልጽ ጽሑፍ በደረቱ ላይ መለጠፍ አለበት፡፡ የመወዳደደሪያ ቁጥር ከኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በቴክኒካል ስብሰባ ቀን ይሰጣል፡፡

## አንቀጽ አስራ አራት
## በስም ጥሪ ቦታ በሰዓት መገኘት

ማንኛውም ተወዳዳሪ ውድድሩ ከመጀመሩ በፊት ቢያንስ ከ45 ደቂቃ በፊት በስም ጥሪ ቦታ በመገኘት ለውድድሩ ዝግጁ መሆኑን ለስም ጠሪ ዳኞች ማሳወቅ ይኖርበታል፤ በስም ጥሪ ቦታ ተገኝቶ ስሙን ለስም ጠሪ ዳኞች ያላሳወቀ አትሌት በውድድሩ ላይ መካፈል አይችልም፤ ተወዳድሮ ቢገኝ ውጤቱ ይሰረዛል፡፡

## አንቀጽ አስራ አምስት
## የተወዳዳሪ ቴሴራ ወይም መታወቂያ

1. አትሌቶች በስም ጥሪ ቦታ ማንነታቸውን የሚገልጽ በዘመኑ በክልሉ/ከተማ አስተዳደሩ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የታደሰ ቴሴራ ወይም ፖስፖርት ይዘው መቅረብ አለባቸው፤ ስርዝ ድልዝ ያለው ቴሴራ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ ቴሴራ የሌለው በውድድሩ ላይ መሳተፍ አይችልም፤
2. በቴሴራው/መታወቂያው ላይ የትውልድ ዘመን መገለጽ አለበት፤

## አንቀጽ አስራ ስድስት
## ሽልማት

1. በእያንዳንዱ የውድድር ተግባር ከ1ኛ-3ኛ ለሚወጡ አትሌቶች በሁለቱም ፆታ የወርቅ፣ የብርና የነሐስ ሜዳሊያ ሽልማት ይሰጣል፤
2. በውድድሩ በቡድን ነጥብ የወንድ አሸናፊ እና የሴት አሸናፊ ለየብቻቸው የዋንጫ ሽልማት ይሰጣል፤
3. የሴትና የወንድ ነጥብ ተደምሮ አብላጫ ነጥብ ላስመዘገበ አጠቃላይ ቡድን የዋንጫ ሽልማት ይሰጣል፤

## አንቀጽ አስራ ሰባት
## ያልተገባ ፀባይ

ማንኛውም ተወዳዳሪ አትሌት፣ አሰልጣኝ፣ የቡድን መሪ፣ ወጌሻ ወይም ሌሎች የቡድን አባላት ውድድሩ በሚከናወንበት ወቅት ያልተገባ ፀባይ ካሣየና ውድድሩን በሚመሩ ዳኞች ወይም የውድድር አዘጋጆች ሪፖርት ቀርቦ ጥፋቱ ከተረጋገጠ በአትሌቲክስ ፌዴሬሽን በተዘጋጀው የአሠልጣኞች፣ አትሌቶችና የክለቦች የሥነ-ምግባር ደንብ አንቀጽ አስር መሠረት ይቀጣል፡፡

## አንቀጽ አስራ ስምንት
## በውድድሩ መክፈቻና መዝጊያ ሥነ-ሥርዓት ላይ መገኘት

1. በውድድሩ ተካፋይ የሚሆኑ ቡድኖች የቡድናቸውን አርማ ይዘው በተሟላ ስፖርታዊ አለባበስ እንዲሁም ባህላዊ አልባሳትን ለብሰው በውድድሩ መክፈቻና መዝጊያ ሥነ-ሥርዓት ላይ መገኘት አለባቸው፤
2. እንደ አስፈላጊነቱ ከውድድር በኋላ በሚደረጉ ቴክኒካል ስብሰባዎች የቡድን መሪዎች/አሠልጣኞች መገኘት አለባቸው፡፡

## *አንቀጽ አስራ ዘጠኝ*

## *የዶፒንግ ምርመራ*

በ፤ኛው የኢትዮጵያ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች አትሌቲክስ ሻምፒዮና የዓለም አቀፉ ፀረ ዶፒንግ ኤጀንሲ እና የኢትዮጵያ ፀረ ዶፒንግ ኦርጋናይዜሽን ሕግና ደንብ በሚፈቅደው መሠረት ከውድድሩ በፊት እና ከውድድሩ በኋላ የዶፒንግ ምርመራ ይከናወናል፡፡

## *አንቀጽ ሀያ*

## *የቴክኒካል ስብሰባ*

የቴክኒካል ስብሰባ የካቲት 25/2011 ዓ.ም ከጠዋቱ 4፡00 በአዲስ አበባ ስታዲየም ይካሄዳል፡፡ በስብሰባው ከየቡድኑ አንድ ቡድን መሪና አንድ አሠልጣኝ ብቻ ይሳተፋሉ፡፡

## *አንቀጽ ሃያ*

## *የክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች ቡድን ኮታ*

1. የትግራይ ክልል 45 ሰው ቡድን መሪና አሰልጣኝን ጨምሮ፤
2. አማራ ክልል 45 ሰው ቡድን መሪና አሰልጣኝን ጨምሮ፤
3. ኦሮሚያ ክልል 45 ሰው ቡድን መሪና አሰልጣኝን ጨምሮ፤
4. ደቡብ ክልል 45 ሰው ቡድን መሪና አሰልጣኝን ጨምሮ፤
5. አዲስ አበባ አስተዳደር 45 ሰው ቡድን መሪና አሰልጣኝን ጨምሮ፤
6. ሐረሪ ክልል 20 ሰው ቡድን መሪና አሰልጣኝን ጨምሮ፤
7. ድሬዳዋ አስተዳደር 20 ሰው ቡድን መሪና አሰልጣኝን ጨምሮ፤
8. ጋምቤላ ክልል 15 ሰው ቡድን መሪና አሰልጣኝን ጨምሮ፤
9. አፋር ክልል 15 ሰው ቡድን መሪና አሰልጣኝን ጨምሮ፤
10. ሱማሌ ክልል 15 ሰው ቡድን መሪና አሰልጣኝን ጨምሮ፤
11. ቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል 25 ሰው ቡድን መሪና አሰልጣኝን ጨምሮ፤

ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ከተሰጣቸው ኮታ ውጪ በራሳቸው ወጪ ተጨማሪ አትሌቶችን በውድድሩ ማሳተፍ የሚችሉ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

# ለ1ኛው የኢትዮጵያ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች አትሌቲክስ ሻምፒዮና በየዉድድር ምድቡ

# የተወዳዳሪዎች መመዝገቢያ ቅጽ

ክልል/ከተማ አስተዳደር ________________________

ፆታ፡ ሴት

| ተ.ቁ. | የውድድሩ ዓይነት | ስም እስከ አያት | በዓመቱ አትሌቷ ያስመዘገበችው ውጤት በሰዓት/በሜትር | የውድድሩ ስም |
|---|---|---|---|---|
| 1. | 100 ሜትር | 1. | | |
| | | 2. | | |
| | | 3. | | |
| | | 4. | | |
| 2. | 200 ሜትር | 1. | | |
| | | 2. | | |
| | | 3. | | |
| | | 4. | | |
| 3. | 400 ሜትር | 1. | | |
| | | 2. | | |
| | | 3. | | |
| | | 4. | | |
| 4. | 800 ሜትር | 1. | | |
| | | 2. | | |
| | | 3. | | |
| | | 4. | | |
| 5. | 1500 ሜትር | 1. | | |
| | | 2. | | |
| | | 3. | | |
| | | 4. | | |
| 6. | 3000 ሜትር መሠናክል | 1. | | |
| | | 2. | | |
| | | 3. | | |
| | | 4. | | |
| 7. | 400 ሜ. መሠናክል | 1. | | |
| | | 2. | | |
| | | 3. | | |
| | | 4. | | |
| 8. | 5000 ሜትር | 1. | | |
| | | 2. | | |
| | | 3. | | |
| | | 4. | | |
| 9. | 10,000 ሜትር | 1. | | |
| | | 2. | | |
| | | 3. | | |
| | | 4. | | |
| 10. | 100 ሜ. መሠናክል | 1. | | |
| | | 2. | | |
| | | 3. | | |
| | | 4. | | |
| 11. | ከፍታ ዝላይ | 1. | | |
| | | 2. | | |
| | | 3. | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | 4. | | |
| 12. | ርዝመት ዝላይ | 1. | | |
| | | 2. | | |
| | | 3. | | |
| | | 4. | | |
| 13. | ሱሉስ ዝላይ | 1. | | |
| | | 2. | | |
| | | 3. | | |
| | | 4. | | |
| 14. | አሎሎ ውርወራ | 1. | | |
| | | 2. | | |
| | | 3. | | |
| | | 4. | | |
| 15. | ዲስከስ ውርወራ | 1. | | |
| | | 2. | | |
| | | 3. | | |
| | | 4. | | |
| 16. | ጦር ውርወራ | 1. | | |
| | | 2. | | |
| | | 3. | | |
| | | 4. | | |
| 17. | 4 X 100 ሜትር | 1. | | |
| | | 2. | | |
| | | 3. | | |
| | | 4. | | |
| | | 5. | | |
| | | 6. | | |
| 18. | 4 X 400 ሜትር | 1. | | |
| | | 2. | | |
| | | 3. | | |
| | | 4. | | |
| | | 5. | | |
| | | 6. | | |
| 19. | 20 ኪሎ ሜትር እርምጃ | 1. | | |
| | | 2. | | |
| | | 3. | | |
| | | 4. | | |

# 1ኛው የኢትዮጵያ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች አትሌቲክስ ሻምፒዮና በየዉድድር ምድቡ

## የተወዳዳሪዎች

## መመዝገቢያ ቅጽ

ክልል/ከተማ አስተዳደር________________________

ፆታ: ወንድ

| ተ.ቁ. | የውድድሩ ዓይነት | ስም ከነአያት | በዓመቱ አትሌቱ ያስመዘገበው ውጤት በሰዓት/በሜትር | የውድድሩ ስም |
|---|---|---|---|---|
| 1. | 100 ሜትር | 1. | | |
| | | 2. | | |
| | | 3. | | |
| | | 4. | | |
| 2. | 200 ሜትር | 1. | | |
| | | 2. | | |
| | | 3. | | |
| | | 4. | | |
| 3. | 400 ሜትር | 1. | | |
| | | 2. | | |
| | | 3. | | |
| | | 4. | | |
| 4. | 800 ሜትር | 1. | | |
| | | 2. | | |
| | | 3. | | |
| | | 4. | | |
| 5. | 1500 ሜትር | 1. | | |
| | | 2. | | |
| | | 3. | | |
| | | 4. | | |
| 6. | 5000 ሜትር | 1. | | |
| | | 2. | | |
| | | 3. | | |
| | | 4. | | |
| 7. | 10,000 ሜትር | 1. | | |
| | | 2. | | |
| | | 3. | | |
| | | 4. | | |
| 8. | 110 ሜ. መሠናክል | 1. | | |
| | | 2. | | |
| | | 3. | | |
| | | 4. | | |
| 9. | 400 ሜ. መሠናክል | 1. | | |
| | | 2. | | |
| | | 3. | | |
| | | 4. | | |
| 10. | 3000 ሜ. መሠናክል | 1. | | |
| | | 2. | | |
| | | 3. | | |
| | | 4. | | |
| 11. | ከፍታ ዝላይ | 1. | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | 2. | | |
| | | 3. | | |
| | | 4. | | |
| 12. | ርዝመት ዝላይ | 1. | | |
| | | 2. | | |
| | | 3. | | |
| | | 4. | | |
| 13. | ሱሉስ ዝላይ | 1. | | |
| | | 2. | | |
| | | 3. | | |
| | | 4. | | |
| 14. | ምርኩዝ ዝላይ | 1. | | |
| | | 2. | | |
| | | 3. | | |
| | | 4. | | |
| 15. | አሎሎ ውርወራ | 1. | | |
| | | 2. | | |
| | | 3. | | |
| | | 4. | | |
| 16. | ዲስከስ ውርወራ | 1. | | |
| | | 2. | | |
| | | 3. | | |
| | | 4. | | |
| 17. | ጦር ውርወራ | 1. | | |
| | | 2. | | |
| | | 3. | | |
| | | 4. | | |
| 18. | መዶሻ ውርወራ | 1. | | |
| | | 2. | | |
| | | 3. | | |
| | | 4. | | |
| 19. | 4 X 100 ሜትር | 1. | | |
| | | 2. | | |
| | | 3. | | |
| | | 4. | | |
| | | 5. | | |
| | | 6. | | |
| 20. | 4 X 400 ሜትር | 1. | | |
| | | 2. | | |
| | | 3. | | |
| | | 4. | | |
| | | 5. | | |
| | | 6. | | |
| 21. | 20 ኪሎ ሜትር እርምጃ | 1. | | |
| | | 2. | | |
| | | 3. | | |
| | | 4. | | |

## 1ኛው የኢትዮጵያ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች አትሌቲክስ ሻምፒዮና በየውድድር ምድቡ የሚሳተፉ አትሌቶች ብዛት ማሰባሰቢያ ቅጽ

ፆታ፡ ሴት

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 100 ሜትር | | 200 ሜትር | | 400 ሜትር | |
| 800 ሜትር | | 1500 ሜትር | | | |
| 5000 ሜትር | | 10,000 ሜትር | | 100 ሜትር መሠናክል | |
| 400 ሜ. መሠናክል | | 3000 ሜትር መሠ. | | 4 X 100 ሜትር | |
| 4 X 400 ሜትር | | 20 ኪሎ ሜትር እርምጃ | | | |
| ከፍታ ዝላይ | | ርዝመት ዝላይ | | ሱሉስ ዝላይ | |
| አሎሎ ውርወራ | | ዲስከስ ውርወራ | | ጦር ውርወራ | |

# 1ኛው የኢትዮጵያ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች አትሌቲክስ ሻምፒዮና

## በየውድድር ምድቡ የሚሳተፉ አትሌቶች ብዛት ማሰባሰቢያ ቅጽ

ፆታ: ወንድ

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 100 ሜትር | | 200 ሜትር | | 400 ሜትር | |
| 800 ሜትር | | 1500 ሜትር | | 5000 ሜትር | |
| 10,000 ሜትር | | 110 ሜ. መሠናክል | | 400 ሜ. መሠናክል | |
| 3000 ሜ. መሠናክል | | 4 X 100 ሜትር | | 4 X 400 ሜትር | |
| ከፍታ ዝላይ | | ምርኩዝ ዝላይ | | ርዝመት ዝላይ | |
| ሱሉስ ዝላይ | | አሎሎ ውርወራ | | ዲስከስ ውርወራ | |
| መዶሻ ውርወራ | | ጦር ውርወራ | | 20 ኪ. ሜትር እርምጃ | |

# በ1ኛው የኢትዮጵያ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች አትሌቲክስ ሻምፒዮና የሚሳተፉ አፊሻሎች መመዝገቢያ ቅጽ

| ተ.ቁ. | ሙሉ ስም | ፆታ | የስራ ኃላፊነት |
|---|---|---|---|
| 1. | | | |
| 2. | | | |
| 3. | | | |
| 4. | | | |
| 5. | | | |
| 6. | | | |
| 7. | | | |
| 8. | | | |
| 9. | | | |
| 10. | | | |

**የመግለጫ፡ -**

1. የቡድን መሪ
2. አሠልጣኝ
3. የቴክኒክ ድጋፍ ስጪ
4. ሐኪም
5. ሌላ የሚመለከታቸው

**ቅጹን የሞላው**

ስምና ፊርማ ___________________

ኃላፊነት ___________________

ቀን ___________________

# በ1ኛው የኢትዮጵያ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች አትሌቲክስ ሻምፒዮና የተሳታፊ ልዑካን ማጠቃለያ መመዝገቢያ ቅጽ

ክልል/ከተማ አስተዳደር______________________

ስልክ ቁጥር ______________ ኢ-ሜል ______________ ፋክስ ______________

| | ወንድ | ሴት | ድምር |
|---|---|---|---|
| ተወዳዳሪዎች | | | |
| የቡድን መሪዎች | | | |
| የቴክኒክ ድጋፍ ሰጪዎች | | | |
| አሰልጣኞች | | | |
| ሐኪም | | | |
| ፊዚዮ ቴራፒስት (ወጌሻ) | | | |
| **ድምር** | | | |

**ቅጹን የሞላው**

ስምና ፊርማ ______________

ኃላፊነት ______________

ቀን ______________

# 1ኛው የኢትዮጵያ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች አትሌቲክስ ሻምፒዮና ፕሮግራም

**1ኛው ቀን የካቲት 26 /2011 ዓ.ም. ጠዋት**

| ሰዓት | የውድድር ተግባር | ፆታ | የውድድር ዓይነት |
|---|---|---|---|
| 2፡00 | አሎሎ ውርወራ | ሴት | ፍፃሜ |
| 2፡35 | ሱሉስ ዝላይ | ወንድ | ፍፃሜ |
| 3፡00 | 10,000 ሜትር | ሴት | ፍፃሜ |
| 3፡50 | 800 ሜትር | ሴት | ማጣሪያ |
| 4፡10 | አሎሎ ውርወራ | ወንድ | ፍፃሜ |
| **4፡10** | **10,000 ሜትር** | **ሴት** | **ሽልማት** |
| 4፡20 | 400 ሜትር | ወንድ | ማጣሪያ |
| **4፡50** | **አሎሎ ውርወራ** | **ሴት** | **ሽልማት** |
| **4፡55** | **ስሱስ ዝላይ** | **ወንድ** | **ሽልማት** |
| 5፡00 | 100 ሜትር | ሴት | ማጣሪያ |
| **5፡30** | **አሎሎ ውርወራ** | **ወንድ** | **ሽልማት** |
| 5፡40 | 100 ሜትር | ወንድ | ማጣሪያ |

**1ኛው ቀን የካቲት 26/2011 ዓ.ም. ከሠዓት**

| ሰዓት | የውድድር ተግባር | ፆታ | የውድድር ዓይነት |
|---|---|---|---|
| **9፡00** | **መክፈቻ** | | |
| 9፡30 | ስሱስ ዝላይ | ሴት | ፍፃሜ |
| 9፡40 | 100 ሜትር | ሴት | ግ/ፍፃሜ |
| 10፡00 | 100 ሜትር | ወንድ | ግ/ፍፃሜ |
| 10፡20 | 400 ሜትር | ወንድ | ግ/ፍፃሜ |
| 10፡40 | 800 ሜትር | ሴት | ግ/ፍፃሜ |
| **11፡00** | **ስሉስ ዝላይ** | **ሴት** | **ሽልማት** |
| **11፡10** | 10,000 ሜትር | **ወንድ** | ፍፃሜ |
| **12፡00** | **10,000 ሜትር** | **ወንድ** | **ሽልማት** |

# 1ኛው የኢትዮጵያ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች አትሌቲክስ ሻምፒዮና ፕሮግራም

## 2ኛው ቀን የካቲት 27 /2010 ዓ.ም. ጠዋት

| ሰዓት | የውድድር ተግባር | ፆታ | የውድድር ዓይነት |
|---|---|---|---|
| 2:30 | ዲስከስ ውርወራ | ሴት | ፍፃሜ |
| 2:40 | 3000 ሜ መሠ | ሴት | ማጣሪያ |
| 3:35 | 400 ሜ መሠ | ሴት | ማጣሪያ |
| 4:05 | 400 ሜ መሠ | ወንድ | ማጣሪያ |
| 4:35 | 800 ሜትር | ወንድ | ማጣሪያ |
| 5:15 | 400 ሜትር | ሴት | ማጣሪያ |
| 5:25 | ዲስከስ ውርወራ | ሴት | ሽልማት |
| 5:35 | 400 ሜትር | ወንድ | ፍፃሜ |
| 5:45 | 800 ሜትር | ሴት | ፍፃሜ |
| **5:55** | **100 ሜትር** | ሴት | ፍፃሜ |
| 6:05 | 400 ሜትር | ወንድ | ሽልማት |
| **6:15** | 100 ሜትር | ወንድ | ፍፃሜ |
| **6:25** | **800 ሜትር** | **ሴት** | **ሽልማት** |
| **6:35** | **100 ሜትር** | **ሴት** | **ሽልማት** |
| **6:45** | **100 ሜትር** | **ወንድ** | **ሽልማት** |

## 3ኛው ቀን የካቲት 28 /2011 ዓ.ም. ከሰዓት

| ሰዓት | የውድድር ተግባር | ፆታ | የውድድር ዓይነት |
|---|---|---|---|
| 9:00 | ዲስከስ | ወንድ | ፍፃሜ |
| 9:05 | ርዝመት ዝላይ | ሴት | ፍፃሜ |
| 9:10 | 100 ሜትር መሠ. | ሴት | ማጣሪያ |
| 9:30 | 110 ሜትር መሠ. | ወንድ | ማጣሪያ |
| 9:50 | 3000 ሜትር መሠ. | ወንድ | ማጣሪያ |
| 10:20 | 1500 ሜትር | ሴት | ማጣሪያ |
| 10:50 | 200 ሜትር | ሴት | ማጣሪያ |
| **11:20** | **ዲስከስ ውርወራ** | **ወንድ** | **ሽልማት** |
| 11:30 | 200 ሜትር | ወንድ | ማጣሪያ |
| **11:50** | **ርዝመት ዝላይ** | **ሴት** | **ሽልማት** |
| 12:00 | 800 ሜትር | ወንድ | ግ/ፍፃሜ |
| 12:15 | 400 ሜትር | ሴት | ግ/ፍፃሜ |

# 1ኛው የኢትዮጵያ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች አትሌቲክስ ሻምፒዮና ፕሮግራም

4ኛው ቀን የካቲት 29 /2010 ዓ.ም. ጠዋት

| ሰዓት | የውድድር ተግባር | ፆታ | የውድድር ዓይነት |
|---|---|---|---|
| 2:30 | ምርኩዝ ዝላይ | ወንድ | ፍፃሜ |
| 2:35 | ርዝመት ዝላይ | ወንድ | ፍፃሜ |
| 2:40 | 5000 ሜትር | ወንድ | ማጣሪያ |
| 3:25 | 1500 ሜትር | ሴት | ግ/ፍፃሜ |
| 3:40 | 1500 ሜትር | ወንድ | ማጣሪያ |
| 4:10 | 5000 ሜትር | ሴት | ማጣሪያ |
| 4:30 | 100 ሜትር መሠ. | ሴት | ግ/ፍፃሜ |
| 4:45 | 110 ሜትር መሠ. | ወንድ | ግ/ፍፃሜ |
| 5:00 | ርዝመት ዝላይ | ወንድ | ሽልማት |
| 5:10 | 200 ሜትር | ሴት | ግ/ፍፃሜ |
| 5:25 | 200 ሜትር | ወንድ | ግ/ፍፃሜ |
| **5:40** | **ምርኩዝ ዝላይ** | **ወንድ** | **ሽልማት** |
| 5:50 | 400 ሜትር መሠ. | ሴት | ግ/ፍፃሜ |
| 6:05 | 400 ሜትር መሠ. | ወንድ | ግ/ፍፃሜ |
| 6:20 | 800 ሜትር | ወንድ | ፍፃሜ |
| 6:30 | 400 ሜትር | ሴት | ፍፃሜ |
| **6:40** | **800 ሜትር** | **ወንድ** | **ሽልማት** |
| **6:50** | **400 ሜትር** | **ሴት** | **ሽልማት** |

5ኛው ቀን የካቲት 30 /2010 ዓ.ም. ከሰዓት

| ሰዓት | የውድድር ተግባር | ፆታ | የውድድር ዓይነት |
|---|---|---|---|
| 9:00 | ከፍታ ዝላይ | ሴት | ፍፃሜ |
| 9:05 | ጦር ውርወራ | ወንድ | ፍፃሜ |
| 9:15 | 200 ሜትር | ሴት | ፍፃሜ |
| 9:25 | 200 ሜትር | ወንድ | ፍፃሜ |
| 9:35 | 3000 ሜትር መሠ. | ሴት | ፍፃሜ |
| **9:50** | **200 ሜትር** | **ሴት** | **ሽልማት** |
| 10:00 | **1500 ሜትር** | ሴት | ፍፃሜ |
| **10:10** | 100 ሜትር መሠ. | ሴት | ፍፃሜ |
| **10:20** | **110 ሜትር መሠ.** | ወንድ | ፍፃሜ |
| **10:30** | **200 ሜትር** | ወንድ | ሽልማት |
| 10:40 | **1500 ሜትር** | ሴት | ፍፃሜ |
| 10:45 | **1500 ሜትር** | ሴት | ሽልማት |
| **10:50** | 400 ሜትር መሠ. | ሴት | ፍፃሜ |
| **11:00** | 400 ሜትር መሠ. | ወንድ | ፍፃሜ |
| **11:10** | **3000 ሜትር መሠ.** | **ሴት** | **ሽልማት** |
| **11:20** | **100 ሜትር መሠ.** | **ወንድ** | ሽልማት |
| **11:30** | 4X100 ሜትር | **ሴት** | ማጣሪያ |
| **11:45** | 110 ሜትር መሠ. | **ወንድ** | **ሽልማት** |
| **11:55** | **400 ሜትር መሠ.** | **ሴት** | **ሽልማት** |
| **12:00** | 4X100 ሜትር | **ወንድ** | ማጣሪያ |
| **12:15** | 400 ሜትር መሠ. | **ወንድ** | **ሽልማት** |
| **12:20** | 4X400 ሜትር | **ሴት** | ማጣሪያ |
| **12:25** | ከፍታ ዝላይ | **ሴት** | **ሽልማት** |
| **12:30** | ጦር ውርወራ | **ወንድ** | **ሽልማት** |
| **12:35** | 4X400 ሜትር | **ወንድ** | ማጣሪያ |

# 1ኛው የኢትዮጵያ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች አትሌቲክስ ሻምፒዮና ፕሮግራም

6ኛው ቀን መጋቢት 01 /2011 ዓ.ም. ጠዋት

| ሰዓት | የውድድር ተግባር | ፆታ | የውድድር ዓይነት |
|---|---|---|---|
| 1:00 | መዶሻ ውርወራ | ወንድ | ፍፃሜ |
| 1:15 | 20 ኪ.ሜ ርምጃ | ሴት | ፍፃሜ |
| 1:30 | 20 ኪ.ሜ ርምጃ | ወንድ | ፍፃሜ |
| 2:00 | ከፍታ ዝላይ | ወንድ | ፍፃሜ |
| 2:05 | ጦር ውርወራ | ሴት | ፍፃሜ |
| 2:10 | 3000 ሜትር መሠ. | ወንድ | ፍፃሜ |
| 2:25 | መዶሻ ውርወራ | ወንድ | ሽልማት |
| 2:35 | 20 ኪ.ሜ ርምጃ | ሴት | ሽልማት |
| 2:45 | 20 ኪ.ሜ ርምጃ | ወንድ | ሽልማት |
| 2:55 | 5000 ሜትር | ወንድ | ፍፃሜ |
| 3:20 | 3000 ሜትር | ወንድ | ሽልማት |
| 3:35 | 1500 ሜትር | ወንድ | ፍፃሜ |
| 3:45 | 5000 ሜትር | ሴት | ፍፃሜ |
| 4:05 | 1500 ሜትር | ወንድ | ሽልማት |
| 4:15 | 5000 ሜትር | ወንድ | ሽልማት |
| 4:25 | 4X100 ሜትር | ሴት | ፍፃሜ |
| 4:35 | 5000 ሜትር | ሴት | ሽልማት |
| 4:45 | 4X100 ሜትር | ወንድ | ፍፃሜ |
| 4:55 | ከፍታ ዝላይ | ወንድ | ሽልማት |
| 5:00 | ጦር ውርወራ | ሴት | ሽልማት |
| 5:05 | 4X400 ሜትር | ሴት | ፍፃሜ |
| 5:15 | 4X100 ሜትር | ሴት | ሽልማት |
| 5:20 | 4X400 ሜትር | ወንድ | ሽልማት |
| 5:30 | 4X100 ሜትር | ወንድ | ሽልማት |
| 5:40 | 4X400 ሜትር | ሴት | ሽልማት |
| የመዝጊያ ፕሮግራም | | | |

*ማሳሰቢያ፡ -*

o *የውድድሩ ፕሮግራም እንደ አስፈላጊነቱ ሊለወጥ ወይም ሊስተካከል ይችላል፡፡*

*የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን*